# የግል ሬዲዮ መገናኛ መመሪያ

የኢትዮጵያ ቴሌኮሙኒኬሽን ኤጀንሲ በሚኒስትሮች ምክር ቤት የቴሌኮሙኒኬሽን አገልግሎት ደንብ ቁጥር 47/1991 አንቀጽ 52 ንዑስ አንቀጽ 3 መሠረት ይህን መመሪያ አውጥቷል፡፡

# ክፍል አንድ

# ጠቅላላ

## ንዑስ ክፍል አንድ

## አጭር ርዕስ፣ ትርጓሜ፣ የተፈፃሚነት ወሰን እና አይ.ቲ.ዩ-አር

1. **አጭር ርዕስ**

ይህ መመሪያ " የኢትዮጵያ ቴሌኮሙኒኬሽን ኤጀንሲ የግል ሬዲዮ መገናኛ መመሪያ ቁጥር 1 /1997 " ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **ትርጓሜ**

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ፣

ሀ. "ኤጀንሲ" ማለት የኢትዮጵያ ቴሌኮሙኒኬሽን ኤጀንሲ ነው፡፡

ለ. "አማተር" ማለት እድሜው 18 የሞላውና አማተር ቋሚ የሬዲዮ መገናኛ ጣቢያ ስራ እንዲያከናውን በኤጀንሲው ፈቃድ የተሰጠው ሰው ነው፡፡

ሐ. "ቋሚ የአማተር የሬዲዮ መገናኛ አገልግሎት" ማለት ለግል ስልጠና፣ እርስ በርስ ለሚደረግ መገናኛ እና ለቴክኒካዊ የምርመራ ሥራ አማተሮች ለግል ጉዳያቸው ብቻ የሚያካሂዱት የግል የሬዲዮ መገናኛ አገልግሎት ነው፡፡



www.chilot.me

መ. “አማተር ቋሚ የሬዲዮ መገናኛ ጣቢያ” ማለት ለአማተር ቋሚ የሬዲዮ መገናኛ አገልግሎት የሚውል የግል የሬዲዮ መገናኛ ጣቢያ ነው::

ሠ. “የአደጋ ጊዜ ጥሪ” ማለት በሰው ህይወት ላይ የማይቀር አደጋ ሊመጣ የሚችል መሆኑን የሚያመለክት ሁኔታ በማጋጠሙ ምክንያት አስቸኳይ የህይወት ማዳን እርዳታ የሚያስፈልግ መሆኑን ለማስታወቅ የሚደረግ የሕይወት ማዳን የሬዲዮ ጥሪ ነው::

ረ. “ቋሚ የሬዲዮ መገናኛ አገልግሎት” ማለት ተለይተው በታወቁ ቋሚ ጣቢያዎች መካከል የሚደረግ የግል የሬዲዮ መገናኛ አገልግሎት ነው:: ይህም ለአውሮፕላን ወይም ለመርከብ ደህንነት ወይም ናቪጌሽን ወይም ሌላ ተግባር ሲባል ተለይተው በታወቁ ቋሚ ጣቢያዎች መካከል የሚደረግ የሬዲዮ መገናኛ አገልግሎትን ያጠቃልላል፡፡

ሰ. “ቋሚ የሬዲዮ መገናኛ ጣቢያ” ማለት ቋሚ የሬዲዮ መገናኛ አገልግሎት የሚውል የግል ሬዲዮ መገናኛ ጣቢያ ነው::

ሸ. “ኢንተርፈረንስ” ማለት በዓለም አቀፍ የቴሌኮሙኒኬሽን ህብረት የሬዲዮ መመሪያ መሠረት (አይ.ቲ.ዩ-አር) እየሰራ የሚገኝ የሬዲዮ መገናኛ አገልግሎትን የመስማት ሁኔታ በከፍተኛ መጠን የሚጎዳ፣ የሚያግድ ወይም በተደጋጋሚ የሚያውክ ወይም በአንድ ወይም በጥምረት የሚወጡ ኤምሽኖች፣ ራዲየሽኖች ወይም ኢንዳክሽኖች ውጤት በሆነ ያልተፈለገ ሀይል ምክንያት የሬዲዮ ናቪጌሽን ተግባር ወይም ሌላ የደህንነት አገልግሎት ተግባርን አደጋ ላይ የሚጥል ነው::

ቀ. “ኢንስፔክተር” ማለት በቴሌኮሙኒኬሽን አዋጅ ቁጥር 49/1989 (እንደተሻሻለው) አንቀጽ 17 መሠረት ኢንስፔክተር ተብሎ የሚመደብ የኤጀንሲው ሠራተኛ ነው::


www.chilot.me

በ. “ፈቃድ” ማለት ተለይቶ በተመደበ የሬዲዮ ፍሪኩዌንሲ መሠረት የግል ሬዲዮ መገናኛ ጣቢያ ባለቤት ለመሆን፣ ለመትከል ወይም ለማካሄድ በኤጀንሲው የሚሰጥ ፈቃድ ነው:: ለአማተር ቋሚ የሬዲዮ መገናኛ ጣቢያ የሚሰጥ ፈቃድን ያጠቃልላል::

ተ. “ባለፈቃድ” ማለት ፈቃድ የተሰጠው ማለት ነው::

ቸ. “ተንቀሳቃሽ የሬዲዮ መገናኛ አገልግሎት” ማለት በተንቀሳቃሽና ቋሚ ጣቢያዎች መካከል ወይም በተንቀሳቃሽ ጣቢያዎች መካከል የሚደረግ የግል የሬዲዮ መገናኛ አገልግሎት ነው:: ይህም በቋሚ የሬዲዮ መገናኛ ጣቢያዎችና በአይሮፕላን ወይም መርከብ መካከል የሚደረግን ሬዲዮ መገናኛ አገልግሎት ያጠቃልላል::

ኀ. “ተንቀሳቃሽ የሬዲዮ መገናኛ ጣቢያ” ማለት ለተንቀሳቃሽ የሬዲዮ መገናኛ አገልግሎት የሚውል በጉዞ እንቅስቃሴ ላይ በመሆን ወይም ከጉዞ እንቅስቃሴው በተፈለገ ቦታ በመቆም ለመጠቀም የሚያስችል የግል ሬዲዮ መገናኛ ጣቢያ ነው::

ነ. “ጊዜያዊ ፈቃድ” ማለት ለማናቸውም ሰው ለኤግዚቢሽን፣ ለዓይነት ማሳያነት ወይም ለሌሎች ተመሳሳይ ዓላማዎች የሬዲዮ መገናኛ መሣሪያዎች ወደ አገር ውስጥ ለማስገባት በኤጀንሲው የሚሰጥ ከአራት ወራት ላልበለጠ ጊዜ የሚያገለግል ጊዜያዊ የፈቃድ ሰነድ ነው::

ኘ. “ሰው” ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው::

አ. “የግል የሬዲዮ መገናኛ አገልግሎት” ማለት ለግል የንግድ ጥቅም ያልዋለ ቋሚ የሬዲዮ መገናኛ አገልግሎት ወይም ተንቀሳቃሽ የሬዲዮ መገናኛ አገልግሎት ነው:: ይህም አማተር ቋሚ የሬዲዮ መገናኛ አገልግሎቶችን በመጠቀም የሚሰጡ አገልግሎቶችን ያጠቃልላል::

ኸ. “የግል የሬዲዮ መገናኛ ጣቢያ” ማለት በግል የሬዲዮ መገናኛ አገልግሎት ውስጥ ጥቅም ላይ የዋለ እያንዳንዱ ቋሚ ወይም ተንቀሳቃሽ ጣቢያ ነው::

ኹ. “ የሬዲዮ መገናኛ” ማለት ከፍተኛ ፍሪኩዌንሲን (ኤችኤፍ)፣ በጣም ከፍተኛ ፍሪኩዌንሲን (ቪ.ኤች.ኤፍ) ወይም አልትራ ሃይ ፍሪኩዌንሲን (ዩ.ኤች.ኤፍ) የሚያካትት በሬዲዮ ሞገድ አማካይነት የሚደረግ የመገናኛ ዓይነት ነው::

ወ. “የስፐሬድ ስፔክትረም መሣሪያ” ማለት ሀ. ከ2.4000 - 2.4835 ጊጋኸርዝ፣
ለ. ከ5.1500 - 5.3500 ጊጋኸርዝ፣ ወይም
ሐ. ከ5.4700-5.7250 ጊጋኸርዝ፣
ውስጥ በሚገኙ የፍሪኩዌንሲ ባንዶች ውስጥ የሚሰራ መሣሪያ ነው::

## 3. የተፈፃሚነት ወሰን

ይህ መመሪያ ለፖሊስ፣ ለሃገር መከላከያና ከሀገር ደህንነት ጋር በቀጥታ በተያያዘ አገልግሎት ላይ የሚውል የሬዲዮ መገናኛ መሣሪያ ባለይዞታ መሆን፣ መትከል ወይም ማካሄድን አይመለከትም::

## 4. የዓለም አቀፍ የቴሌኮሙኒኬሽን ህብረት የሬዲዮ መመሪያ

የኤሮኖቲካል አገልግሎቶችን እና የማሪታይም አገልግሎቶችን የሚመለከቱ ድንጋጌዎችን ጨምሮ አግባብነት ያላቸው የዓለም አቀፍ የቴሌኮሙኒኬሽን ህብረት የሬዲዮ መመሪያ (አይ.ቲ.ዩ-አር) ድንጋጌዎች በዚህ መመሪያ ውስጥ ተፈፃሚነት ይኖራቸዋል::


www.chilot.me

## ንዑስ ክፍል ሁለት

## ስለፈቃድና የባለፈቃዱ ግዴታዎች

### 5. ፈቃድ ስለሚሰጥባቸው የጣቢያ አይነቶችና ስለቴክኒክ ብቃት ማረጋገጫ

ሀ. በዚህ መመሪያ መሠረት ፈቃድ የሚሰጠው ለቋሚ የሬዲዮ መገናኛ ጣቢያ፣ ለተንቀሳቃሽ የሬዲዮ መገናኛ ጣቢያ ወይም ለአማተር ቋሚ ሬዲዮ መገናኛ ጣቢያ ነው፡፡

ለ. የሬዲዮ መገናኛ መሣሪያዎችን በኤግዚቢሽን መልክ ለማቅረብ፣ ለዓይነት ማሳያነት፣ ወይም ለሌላ ተመሳሳይ ተግባር ወደ ሀገር ውስጥ ለማስገባት ኤጀንሲው ጊዜያዊ ፈቃድ ሊሰጥ ይችላል፡፡

ሐ. ኤጀንሲው የቴክኒክ ብቃት ማረጋገጫ ለስፐሬድ ስፔክትረም መሣሪያዎች ይሰጣል፡፡

### 6. ስለፈቃድ ወይም ጊዜያዊ ፈቃድ አስፈላጊነት

#### 6.1 ጠቅላላ

ሀ. የግል ሬዲዮ መገናኛ ጣቢያ ባለይዞታ ለመሆን፣ ለመትከል ወይም ለማካሄድ ከኤጀንሲው ፈቃድ ማግኘት ያስፈልጋል፡፡

ለ. ለአማተር ቋሚ ሬዲዮ መገናኛ ጣቢያ ካልሆነ በስተቀር ለግለሰብም ሆነ ለግላዊ ጥቅም የሬዲዮ መገናኛ መሣሪያዎችን ወደ ሃገር ውስጥ ለማስገባት ፈቃድ አይሰጥም፡፡

ሐ. የሬዲዮ መገናኛ መሣሪያዎችን በኤግዚቢሽን መልክ ለማቅረብ፣ ለዓይነት ማሳያነት ወይም ለሌላ ተመሳሳይ ተግባር ወደ ሃገር ውስጥ ለማስገባት ከኤጀንሲው ጊዜያዊ ፈቃድ ማግኘት ይገባል፡፡

መ. ጊዜያዊ ፈቃድ በማግኘት ወደ ሃገር ውስጥ የገቡ የሬዲዮ መገናኛ መሣሪያዎች ለቋሚ አገልግሎት ሃገር ውስጥ እንዲቆዩ ለማድረግ አይቻልም፡፡


www.chilot.me

ሠ. አግባብነት ያላቸው የዚህ መመሪያ አንቀጽ 10 ድንጋጌዎች ጊዜያዊ ፈቃድ ባገኘ ባለፈቃድ ላይ ተፈፃሚ ይሆናሉ።

6.2 ለፈቃድ ወይም ጊዜያዊ ፈቃድ ስለማመልከት

ሀ. ፈቃድ ለማግኘት የሚቀርብ ማመልከቻ የዚህ መመሪያ አባሪ I ሆኖ የተዘጋጀውን ቅጽ በመሙላት ለኤጀንሲው መቅረብ ይኖርበታል።

ለ. ከላይ በንዑስ አንቀጽ 6.2 (ሀ) መሠረት የግል ሬዲዮ መገናኛ ጣቢያ ፈቃድ እንዲሰጠው የሚቀርብ አመልካች የሚከተሉትን ሁኔታዎች የማሟላት ግዴታ አለበት፤

i. ወደ አገር ውስጥ የሚያስገባው የሬዲዮ መገናኛ መሣሪያ ኤጀንሲው የሚወስነውን የቴክኒክ ደረጃ የሚያሟላ መሆኑን ፣
ii. በዚህ መመሪያ አባሪ III ላይ የተመለከቱትን አግባብነት ያላቸው ሰነዶች በማያያዝ ማመልከቻ ማቅረብ ያለበት መሆኑን፣ እና
iii. ማመልከቻው ለአማተር ቋሚ የሬዲዮ መገናኛ ጣቢያ ፈቃድ ከሆነ በአማተር ሬዲዮ ኦፕሬሽን ወይም በአጠቃላይ የሬዲዮ ኦፕሬሽን የተሰጠውን ሰርቲፊኬት ማቅረብ።

ሐ. የሬዲዮ መገናኛ መሣሪያ ለማስመጣት የሚፈልግ አመልካች በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 6.2 (ሀ) እና (ለ) የተመለከተውን ሁኔታ ሲያሟላ ኤጀንሲው የቅድሚያ ፈቃድ ሊሰጠውና ፍሪኩዌንሲም ሊመድብለት ይችላል። ይህ የቅድሚያ ፈቃድና የፍሪኩዌንሲ ምደባ የሚያገለግለው ቅድሚያ ፈቃድ ከተሰጠበት ቀን ጀምሮ ላሉት ስድስት ወራት ጊዜ ብቻ ነው።

መ. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 6.2 (ሐ) መሠረት የቅድሚያ ፈቃድ የተሰጠ ውና የፍሪኩዌንሲ ምደባ የተደረገለት የሬዲዮ መገናኛ መሣሪያ ወደአገር ውስጥ ከመግባቱ በፊት በቅድሚያ ፈቃዱ መሠረት የመጣ ለመሆኑ በኤጀንሲው ታይቶ መረጋገጥ አለበት።

ሠ. ከላይ በንዑስ አንቀፅ 6.2 (ለ) ላይ የተመለከቱት ሁኔታዎች መሟላታቸው ከተረጋገጠና የሬዲዮ መገናኛ መሣሪያው ከመተከሉ በፊት


www.chilot.me

ለኤጀንሲው ቀርቦ በተመደበለት ፍሪኩዌንሲ መሠረት ኘሮግራም ከተደረገ በኋላ ኤጀንሲው ፈቃድ ይሰጣል፡፡

ረ. ጊዜያዊ ፈቃድ ለማግኘት የሚቀርብ አመልካች የሬዲዮ መገናኛ መሣሪያዎችን ወደ ሀገር ውስጥ ለማስገባት የሚፈልግበትን ምክንያት፣ ለምን ያህል ጊዜ ሃገር ውስጥ እንደሚቆዩና ከሃገር የሚያስወጣበትን ቀን በመግለጽ አግባብነት ካላቸው ማስረጃዎች ጋር አያይዞ ማቅረብ ይኖርበታል፡፡

ሰ. አግባብነት ያላቸው የዚህ ንዑስ አንቀፅ 6.2 ድንጋጌዎች ተፈፃሚነት እንደተጠበቀ ሆኖ፣ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 6.2 (ረ) ላይ የተመለከቱትን ሁኔታዎች ያላሟላ የጊዜያዊ ፈቃድ አመልካች ጊዜያዊ ፈቃዱ አይሰጠውም፡፡

6.3 የሬዲዮ ፍሪኩዌንሲ ምደባና አጠቃቀም

ሀ. ማንኛውም የሬዲዮ መገናኛ ፈቃድ አመልካች በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 6.2 (ለ) ላይ የተዘረዘሩትን ሁኔታዎች ካላሟላ የሬዲዮ መገናኛ መሣሪያውን ወደ አገር ውስጥ ማስገባት አይችልም፡፡

ለ. ለስፐሬድ ስፔክትረም መሣሪያ ካልሆነ በስተቀር የሬዲዮ መገናኛ ጊዜያዊ ፈቃድ እንዲሰጠው የሚቀርብ አመልካች መጠቀም ያለበት በኤጀንሲው የተመደበለትን ፍሪኩዌንሲ ብቻ ነው፡፡

ሐ. ለፍሪኩዌንሲ ምደባ በቀረቡ ማመልከቻዎች ላይ ውሳኔ የሚሰጠው ኤጀንሲው ነው፡፡ ሌሎች ተጨማሪ መመዘኛዎች መኖራቸው እንደተጠበቀ ሆኖ ውሳኔው የኤጀንሲውን የፍሪክዌንሲ ምደባ ሰንጠረዥ እና የሬዲዮ ስፔክትረምን ውጤታማ አጠቃቀም ያገናዘበ መሆን ይገባዋል፡፡

መ. ፍሪኩዌንሲው ተለይቶ ለአንድ ለተወሰነ አገልግሎት የተመደበ ካልሆነ በስተቀር ማንኛውም ፍሪኩዌንሲ “መጀመሪያ የመጣ መጀመሪያ አገልግሎት ያገኛል” የሚል መርህ በመከተል በጋራ ለተለያዩ ተጠቃሚዎች ወይም ለአንድ ተጠቃሚ በግል ይመደባል፡፡ ይሁንና ለህዝብ ጥቅም ሲባል እና የቀረበው ጥያቄ በኤጀንሲው ተቀባይነት ሲያገኝ ኤጀንሲው ለአንድ


www.chilot.me

ተጠቃሚ ተመድቦ የነበረን ፍሪኩዌንሲ መልሶ በመውሰድ ለሌላ አዲስ ተጠቃሚ ሊመድበው ይችላል፡፡ ይኸውም ተፈፃሚ የሚሆነው፡-

i. ለተጠቃሚው ሊመደብ የሚችል አዲስ ፍሪኩዌንሲ ሲኖር እና/ወይም
ii. ይጠቀምበት የነበረው ፍሪኩዌንሲ እንዲመለስ በመደረጉ ምክንያት በተጠቃሚው ላይ የደረሰ ጉዳት ካለ ፍሪኩዌንሲውን የጠየቀው አዲሱ ተጠቃሚ ሊክሰው ከቻለ ነው፡፡

ሠ. ኤጀንሲው መስማማቱን በጽሑፍ ካልገለፀ በቀር በተመደበ ፍሪኩዌንሲ የመጠቀም መብት በሙሉ ወይም በከፊል ለሌላ ወገን ሊተላለፍ አይችልም፡፡

ረ. የፍሪኩዌንሲ ምደባ የሚያገለግለው ለአንድ ዓመት ነው፡፡ በየዓመቱ ፍሪኩዌንሲው የተመደበበት ወይም የታደሰበት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የበጀት ዘመን ካበቃ በኋላ ተገቢውን ክፍያ በመክፈል መታደስ አለበት፡፡

ሰ. የስፕሬድ ስፔክትረም መሣሪያው ለአንድ ተጠቃሚ ብቻ ባልተወሰነ ሁኔታ በዚህ መመሪያ መሠረት በተወሰኑት ፍሪኩዌንሲዎች ወይም የፍሪኩዌንሲ ባንዶች ላይ መሥራት አለበት፡፡

## 7. <u>ፈቃድ ስለመመለስ</u>

ሀ. ባለፈቃዱ የሚፈለግበትን የፈቃድ እና የፍሪኩዌንሲ ክፍያ አጠቃሎ በመክፈል ፈቃዱን ለመመለስ ይችላል፡፡ በዚህ ፈቃዱ በተሰረዘው ጣቢያ ፍሪኩዌንሲ የሚጠቀሙ ሌሎች የግል የሬዲዮ መገናኛ ጣቢያ ፈቃዶች በሙሉ ለኤጀንሲው የተመለሱ ከሆነ የተመደበው ፍሪኩዌንሲ ሊሰረዝ ይችላል፡፡

ለ. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (ሀ) መሠረት ፈቃዱ ተመላሽ ከመደረጉ በፊት ጥቅም ላይ ሲውል የቆየው የሬዲዮ መገናኛ መሣሪያ በኤጀንሲው ሊታሸግ፣ ወይም ከኤጀንሲው ቅድሚያ ፈቃድ በማግኘት ከአገር እንዲወጣ ሊደረግ ወይም ለሦስተኛ ወገን ሊተላለፍ ይችላል፡፡



www.chilot.me

## 8. የፈቃድ ክፍያዎች

የፈቃድና የፍሪኩዌንሲ ክፍያዎች መጠን በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የመሠረተ ልማት ሚኒስቴር መመሪያ መሠረት ይወሰናል፡፡

## 9. ስለፈቃድ ይዘት

በኤጀንሲው የሚሰጥ የግል የሬዲዮ መገናኛ ጣቢያ ፈቃድ ቢያንስ የሚከተሉትን መያዝ አለበት፡፡

ሀ. የባለፈቃዱን ስም

ለ. በሥራ ላይ የዋለው ፍሪኩዌንሲ ወይም የፍሪኩዌንሲ ባንድ

ሐ. ለጣቢያው የተፈቀደለት ኮል ሳይን

መ. የአገልግሎቱ ዓይነት

ሠ. የሚያመነጨው ኤሚሽን ዓይነት

ረ. ማስተላለፊያው የሚያወጣው ከፍተኛ የሃይል መጠን

ሰ. የማስተላለፊያና መቀበያው መሣሪያ ዓይነትና ሰሪው

ሸ. የአንቴናው ዓይነት

ቀ. የግል ሬዲዮ መገናኛ ጣቢያው የሚገኝበት ሥፍራ

በ. የመቀበያው አካባቢ

ተ. የሚሰራበት ሰዓት፡፡

## 10. የባለፈቃዱ ግዴታ

ሀ. ባለፈቃዱ የዚህን መመሪያ ድንጋጌዎች ማክበር አለበት፡፡

ለ. የፈቃድ ካርዱ የግል ሬዲዮ መገናኛ ጣቢያው በሚገኝበት ሥፍራ መቀመጥ አለበት፡፡

ሐ. ባለፈቃዱ ኤጀንሲው ፈቃድ ባልሰጠባቸው የሬዲዮ መገናኛ መሣሪያዎች ወይም ባልተመደበለት ፍሪኩዌንሲ ለመጠቀም አይችልም፡፡

መ. ኤጀንሲው በቅድሚያ በጽሑፍ ካልፈቀደ በቀር ማንም ባለፈቃድ በማናቸውም መንገድ የሬዲዮ መገናኛ መሣሪያዎችን ባለይዞታነት ወይም ባለቤትነት ለሌላ ማስተላለፍ አይችልም፡፡



www.chilot.me

ሠ. ባለፈቃዱ የሬዲዮ መገናኛ መሣሪያው ቢጠፋበት ወይም ቢሰረቅበት በተቻለ ፍጥነት በአቅራቢያው ለሚገኝ የፖሊስ ጣቢያ እና ለኤጀንሲው ስለጉዳዩ ሪፖርት የማድረግ ግዴታ አለበት፡፡

ረ. ባለፈቃዱ ሬዲዮ መገናኛ መሣሪያው እንዲጠቀሙበት ወይም በይዞታቸው ሥር እንዲሆን ባልተፈቀደላቸው ሌሎች ሦስተኛ ወገኖች እጅ እንዳይገባ ተገቢውን ጥንቃቄ የማድረግ ግዴታ አለበት፡፡

ሰ. ባለፈቃዱ በግል ሬዲዮ መገናኛ ጣቢያው ወይም መሣሪያው አግባብ ያለው ሥልጠና ወይም ልምድ የሌላቸው ሰዎች እንዲሰሩበት መፍቀድ የለበትም፡፡

ሸ. ባለፈቃዱ ኤጀንሲው በፈቀደለት ኮል ሳይን ብቻ መጠቀም ይኖርበታል፡፡

ቀ. የግል ሬዲዮ መገናኛ ጣቢያውን ወይም መሣሪያውን በተመለከተ ኤጀንሲው ለሚያቀርባቸው ጥያቄዎች ባለፈቃዱ ትክክለኛውን መረጃ ሳይዘገይ መስጠት ይኖርበታል፡፡

በ. በኤጀንሲው በቅድሚያ በጽሑፍ ካልተፈቀደ በቀር ባለፈቃዱ የሬዲዮ መገናኛ ጣቢያውን ወደ አዲስ ሥፍራ ወይም አካባቢ ማዛወር፣ ወይም በፈቃዱ ላይ ከተመለከተው ወይም ከቀረበው መረጃ በተለየ ሁኔታ ማናቸውም ዓይነት የምዝገባ ዳታ ለውጥ ማድረግ አይችልም፡፡

ተ. ባለፈቃዱ ኤጀንሲው ከፈቀደለት ጂኦግራፊያዊ ሥፍራ ወይም የመጠቀሚያ ሰዓት ውጭ በግል የሬዲዮ መገናኛ ጣቢያው መጠቀም አይችልም፡፡

ቸ. ግልጽ በሆነ ሁኔታ ኤጀንሲው ካልፈቀደ በቀር ማናቸውም ባለፈቃድ በዚህ መመሪያ ከተወሰነው የሃይል መጠን በላይ የሬዲዮ መገናኛ መሣሪያውን የሃይል መጠን ማጉላት ወይም የሃይል መጠኑን መጨመር አይችልም፡፡

ኀ. ባለፈቃዱ በጣቢያው ውስጥ የሚገኙ የሬዲዮ መሣሪያዎችን ከቴክኒክ አኳያ ተገቢ ነው ተብሎ በሚታወቅ አያያዝ ሁኔታ እንዲጠበቁ ማድረግ አለበት፡፡



www.chilot.me

ነ. ባለፈቃዱ የሬዲዮ ሲግናሎችን ወደ ቴሌኮሙኒኬሽን ኔትወርክ ወይም አገልግሎቶች ለማስተላለፍ ወይም ለመለወጥ የሚያስችለው የማገናኛ መሣሪያ ማገናኘት አይችልም፡፡

## 11. ስለፈቃድ እድሳት

ባለፈቃዱ ፈቃዱ የተሰጠበት ወይም የታደሰበት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ሪፑብሊክ የበጀት ዓመት ካበቃ በኋላ በዚህ መመሪያ አባሪ III ላይ የተመለከቱትን ተፈላጊ ሁኔታዎች በማሟላት በየዓመቱ ፈቃዱን ማሳደስ ይገባዋል፡፡

## 12. ፈቃድን ስለማገድ ወይም ስለመሰረዝ

ሀ. ባለፈቃዱ በዚህ መመሪያ ውስጥ የተመለከቱትን ማናቸውንም ድንጋጌዎች ተላልፎ የተገኘ እንደሆነ የእርምት እርምጃ እስኪወስድ ድረስ ኤጀንሲው ፈቃዱን አግዶ ለማቆየት ይችላል፡፡

ለ. ኤጀንሲው የፈቃድ ማገድ እርምጃ የወሰደበትን ምክንያት እና ባለፈቃዱ የተፈጠ ረውን ስህተት ከኤጀንሲው ማስታወቂያ በደረሰው በ15 ቀናት ጊዜ ውስጥ ለማረም መውሰድ ያለበትን እርምጃ ለባለፈቃዱ በፅሁፍ መግለፅ አለበት፡፡

ሐ. ባለፈቃዱ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (ለ) ላይ በተመለከተው መሠረት ኤጀንሲው በሰጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ የተፈጠረውን ስህተት ለማረም ካልቻለ ወይም መታገዱን ችላ በማለት የሬዲዮ መገናኛ ሥራውን የቀጠለ እንደሆነ ኤጀንሲው ፈቃዱን ይሰርዛል፡፡

መ. ባለፈቃዱ ፈቃዱን ያገኘው በሀሰተኛ ወይም በተጭበረበረ ሰነድ መሆኑን ኤጀንሲው ካረጋገጠ ወይም ባለፈቃዱ ከከሰረ ወይም ሥራውን ከተወ ኤጀንሲው ፈቃዱን ይሰርዛል፡፡

ሠ. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (ሐ) ወይም (መ) መሠረት ፈቃዱ ከመሰረዙ በፊት ጥቅም ላይ ሲውል የቆየው የግል የሬዲዮ መገናኛ ጣቢያው በኤጀንሲው ሊታሸግ፣ ወይም ከኤጀንሲው ቅድሚያ ፈቃድ በማግኘት ከአገር እንዲወጣ ለማድረግ ወይም ለሦስተኛ ወገን ለማስተላለፍ ይቻላል፡፡



www.chilot.me

# ንዑስ ክፍል ሦስት
# መሟላት የሚገባቸው ቴክኒካዊ ባህሪያት

13 **በኤች.ኤፍ፣ ቪ.ኤች.ኤፍ እና ዩ.ኤች.ኤፍ ውስጥ ስለሚገኙ የሬዲዮ መገናኛዎች ማሟላት ያለባቸው ቴክኒካዊ ባህሪያት፣**

ሀ. የሬዲዮ ሞገድ ሥርጭት ለኤች.ኤፍ ባንድ የሰማይ ሞገድና በከፊል የምድር ሞገድ እና ለቪ.ኤች.ኤፍ እና ለዩ.ኤች.ኤፍ ባንዶች ደግሞ የሕዋ ሞገድ መሆን ይኖርበታል፡፡

ለ. የቤዝ ባንዱ ሲግናል ድምጽ ወይም ዳታ ሊሆን ይችላል፡፡

ሐ. የኤች.ኤፍ ባንድ ቤዝ ባንድ ሲግናል ድምጽ ከሆነ ሞጁሌሽኑ ሲንግል ሳይድ ባንድ (ኤስ.ኤስ.ቢ.) አምኘሊትዩድ ሞጁሌሽን (ኤ.ኤም) መሆን አለበት፡፡

መ. የቪ.ኤች.ኤፍ እና የዩ.ኤች.ኤፍ ቤዝ ባንዶች ሲግናል ድምጽ ከሆነ ሞጁሌሽኑ ፍሪክዌንሲ ሞጁሌሽን /ኤፍ.ኤም/ መሆን ይኖርበታል፡፡ በኤሮኖቲካል የሬዲዮ ግንኙነት ጊዜ ለቪ.ኤች.ኤፍ. ባንዶች ሞዲሌሽኑ አምፕሊቲዩድ ሞዱሌሽን (ኤ.ኤም) ሊሆን ይችላል፡፡

ሠ. የቤዝ ባንዱ ሲግናል ዳታ ከሆነ ሞጁሌሽኑ ለሁሉም ባንዶች የሚያገለግል ዲጂታል ሞጁሌሽን ቴክኒክ መሆን አለበት፡፡

ረ. የኤች.ኤፍ ባንድ ኦኘሬሽን ሞድ ግማሽ ዱፕሌክስ ለድምጽ መገናኛና ዱኘሌክስ ለዳታ መገናኛ መሆን ይኖርበታል፡፡

ሰ. የቪ.ኤች.ኤፍ እና የዩ.ኤች.ኤፍ ባንዶች ኦፕሬሽን ሞድ ግማሽ ዱኘሌክስ ለድምጽ ግንኙነት፣ ዱፕሌክስ ለዳታ ግንኙነት መሆን ይኖርበታል፡፡

ሸ. ግልጽ በሆነ ሁኔታ ኤጀንሲው ካልፈቀደ በቀር የኤች.ኤፍ ሬዲዮ ማሰራጪያ መግሪያ ሃይል ከ125 ዋት ፒክ ኤንቨሎኘ ፓወር (ፒ.ኢ.ፒ) መብለጥ የለበትም፡፡



www.chilot.me

ቀ. ስፓሪየስ ኤሚሽኑ ከ2nW በላይ መብለጥ እንደሌለበት ባለፈቃዱ ማረጋገጥ አለበት፡፡

## 14. በስኘሬድ ስፔክትረም መሣሪያዎች ላይ መሟላት የሚገባቸው ቴክኒካዊ ባህርያት

የሚከተሉት ቴክኒካዊ ባህርያት በስኘሬድ ስፔክትረም መሣሪያዎች ላይ ተፈፃሚነት ይኖራቸዋል፡፡

ሀ. መሣሪያው ዳይሬክት ሲክዌንስ ስኘሬድ ስፔክትረም (ዲ.ኤስ.ኤስ.ኤስ) ወይም ፍሪክዌንሲ ሆፒንግ ስኘሬድ ስፔክትረም (ኤፍ.ኤች.ኤስ.ኤስ) ወይም ሁለቱንም ያጣመረ ሞጁሌሽን ቴክኒክ ወይም ፊዚካል ሌየር ቴክኖሎጂ መጠቀም ይኖርበታል፡፡

ለ. በኢትዮጵያ ውስጥ ጥቅም ላይ የሚውለው መሣሪያ ለቤት ውስጥ አገልግሎት የተዘጋጀ መሆን ይኖርበታል፡፡

ሐ. የሚፈቀደው ከፍተኛው የማስተላለፊያ ሃይል 100 mW(mean e.i.r.p.) ወይም -10dBW ብቻ ነው፡፡

መ. ፍሪኩዌንሲ ሆፒንግ ስኘሬድ ስፔክትረም ለሚጠቀሙ መሣሪያዎች በአንድ ቻናል የሚኖረው የቆይታ ጊዜ ከ400m/sec መብለጥ አይኖርበትም፡፡

ሠ. ለፍሪኩዌንሲ ሆፒንግ ስኘሬድ ስፔክትረም አነስተኛው e.i.r.p ዴንሲቲ ከ10mW/MHz መብለጥ አይኖርበትም፡፡

ረ. የስኘሬድ ስፔክትረም መሣሪያውን የሬዲዮ ሽፋን ስፋት ለመጨመር ሲባል አቀባባይ ጣቢያ መጠቀም አይቻልም፡፡



www.chilot.me

# ክፍል ሁለት
# ስለ አማተር ቋሚ የሬዲዮ መገናኛ ጣቢያ እና ስለስኘሬድ ስፔክትረም መሣሪያዎች ልዩ ሁኔታዎች

## ንዑስ ክፍል አንድ
## አማተር ቋሚ የሬዲዮ መገናኛ ጣቢያዎች

### 15. አማተር ቋሚ የሬዲዮ ጣቢያዎችን ስለሚመለከቱ ሁኔታዎች

ሀ. በአማተር ቋሚ የሬዲዮ ጣቢያ ከባለፈቃዱ በስተቀር ሌላ ማንም ሰው ሊጠቀምበት አይችልም፡፡

ለ. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀጽ (ሐ) የተመለከተው እንደተጠበቀ ሆኖ አማተር ቋሚ የሬዲዮ ጣቢያ ከሌላ አማተር ቋሚ የሬዲዮ ጣቢያ በስተቀር ከሌላ ማናቸውም ጣቢያ ጋር ግንኙነት ማድረግ የለበትም፡፡

ሐ. በሰው ህይወት ላይ አደጋ እንዳይደርስ ለመከላከልና እርዳታ ለማድረግ ወይም በአስቸኳይ የአደጋ ጊዜ እርዳታ ለመጠየቅ ከማናቸውም ጣቢያዎች ጋር የአስቸኳይ አደጋ ጥሪ ግንኙነት ማድረግ የተፈቀደ ነው፡፡

መ. በአማተር ቋሚ የሬዲዮ ጣቢያዎች አማካይነት የሚደረጉ ግንኙነቶች ግልፅ በሆነ ቋንቋ መከናወን ይኖርባቸዋል፡፡ በእንደዚህ አይነት ግንኙነቶች ጊዜ የሚነገሩት ማናቸውም ቃላትና አገላለጾች በቋንቋው ውስጥ የሚሰጣቸውን የተለመደ ፍቺ መያዝ ይኖርባቸዋል፡፡ የምስጢር ኮድ መጠቀም የተከለከለ ነው፡፡


www.chilot.me

ሠ. ማንም ሰው የሽቀጥ፣ የአገልግሎት ወይም የሌላ ማናቸውም ዓይነት ማስታወቂያ ለመሥራት ወይም ዜና ወይም ሙዚቃ በአማተር ቋሚ የራዲዮ ጣቢያ አማካይነት ለማስተላለፍ አይችልም።

ረ. አማተር ቋሚ የራዲዮ ጣቢያዎች ሽልማት ወይም ሌላ የገንዘብ ጥቅም ለማግኘት የሚያስችል ስርጭት ለማድረግ ወይም መልዕክት ለመቀበል ጥቅም ላይ መዋል የለባቸውም።

ሰ. የአማተር ራዲዮ ባለፈቃድ እያንዳንዱን መልዕክት የሚያስተላልፍበትን ቀንና ሰዓት፣ የተጠቀመውን የፍሪኩዌንሲ ባንድ፣ ለጣቢያው የተፈቀደለትን መጠሪያ ስም፣ የተጠቀመበትን ሃይል መጠን፣ የማስተላለፉን ሥራ የሚሰራውን ሰው ሥምና ሙሉ አድራሻ፣ የተላለፈውን መልዕክት በአጭሩ እና የማስተላለፍ ስራው የሚሄድበትን ሥፍራ አድራሻ የሚመዘግብበት መዝገብ መያዝ ይኖርበታል። ባለፈቃዱ በእያንዳንዱ ምዝገባ ላይ ፊርማውን ማኖር ይኖርበታል።

ሸ. መዝገቡ በጣቢያው ውስጥ ሆኖ ኤጀንሲው በጠየቀ ጊዜ መቅረብ የሚኖርበት ሲሆን በመዝገቡ ላይ ኤጀንሲው ማስታወሻ ሊያሰፍርበት ይችላል። መዝገቡ ስለጣቢያው ሁኔታ በመጨረሻ ከተመዘገበበት ቀን ጀምሮ እስከ ሁለት ዓመት ድረስ ሳይበላሽ በአግባቡ ተይዞ መቀመጥ አለበት።

ቀ. በአማተር ቋሚ የራዲዮ ጣቢያ አገልግሎት ላይ የሚውል የማስተላለፊያ መሣሪያ በማናቸውም ጊዜ ወይም ሁኔታ ከኤጀንሲው ለባለፈቃዱ ከተሰጠው ፍሪኩዌንሲ ውጪ ሌላ ፍሪኩዌንሲ ጋር እንዲገናኝ መደረግ የለበትም።

በ. የአማተር ራዲዮ ባለፈቃዱ በሃገር ደህንነት ላይ ጉዳት ሊያስከትል የሚችል፣ ወይም ከህግ፣ ከህዝብ ሥርዓትና ልማድ ተፃራሪ የሆነ፣ ወይም የውጭ መንግሥትን የሚቃወም ማናቸውም ዓይነት ሲግናል ወይም መልዕክት ማስተላለፍ አይኖርበትም። የአማተር ራዲዮ ስርጭት የሕዝብን ወይም ወታደራዊ አገልግሎትን የሚያውክ በሆነ ጊዜ የታወከው ጣቢያ ወይም ተቆጣጣሪ ክፍል ስለዚሁ ጉዳይ ሲገልጽ ስርጭቱ ወዲያውኑ እንዲቋረጥ ይደረጋል።


www.chilot.me

ተ. የአማተር ራዲዮ ማስተላለፊያ መሣሪያ የሚያወጣው ሃይል ከአንቴናው በፊት በሚኖረው የመጨረሻ ደረጃ መያያዣ ላይ ከ100ዋት መብለጥ አይኖርበትም፡፡

ቸ. የማስተላለፊያ መሣሪያውን የመሥራት ሁኔታና የሚያወጣውን ሃይል ትክክለኛ መሆን ለማወቅና ለማረጋገጥ አማተር ቋሚ የራዲዮ ጣቢያው በመለያና በመቆጣጠሪያ መሣሪያዎች መደራጀት አለበት፡፡

# ንዑስ ክፍል ሁለት

# የስፕሬድ ስፔክትረም መሣሪያዎች

## 16. ጠቅላላ

ሀ. የስኘሬድ ስፔክትረም መሣሪያዎች እንደ ሬዲዮ ሎካል ኤርያ ኔትወርኮች፣ ዋየርለስ ፐርሰናል ኤርያ ኔትወርኮች፣ ሌሎች ለቤት ውስጥ አካባቢ የቅርብ ርቀት መጠቀሚያነት በሚውሉ መሣሪያዎች ባሉ የዋየርለስ ሎካል ኤርያ ኔትወርኮች ላይ እና የIEEE የኮሙኒኬሽን ስታንዳርድ ባላቸው የIEEE 802.11 ስብስቦች እንዲሁም ብሉቱዝ መሣሪያዎች ላይ ሊያገለግሉ ይችላሉ፡፡

ለ. የሬዲዮ መገናኛ መሣሪያዎቹ ለህንፃዎች የውስጥ ለውስጥ አገልግሎትና ለቅርብ አካባቢ ሥራዎች ብቻ ጥቅም ላይ ሊውሉ ይገባል፡፡

ሐ. የስኘሬድ ስፔክትረም መሣሪያዎች ለንግድ አገልግሎት ወይም ለርቀት አካባቢ ኔትወርክ (Wide Area Network) ተግባር ጥቅም ላይ ሊውሉ አይችሉም፡፡

## 17. ለቴክኒክ ብቃት ማረጋገጫ ስለማመልከት

ሀ. ማናቸውም የስኘሬድ ስፔክትረም መሣሪያ ወደ አገር ውስጥ ለማስገባት የሚፈልግ ሰው የቴክኒክ ብቃት ማረጋገጫ እንዲሰጠው ለኤጀንሲው ማመልከት አለበት፡፡


www.chilot.me

ለ. የስኘሬድ ስፔክትረም መሣሪያ የቴክኒክ ብቃት ማረጋገጫ ለማግኘት የሚቀርብ አመልካች በዚህ መመሪያ አባሪ II የተገለፀውን ቅፅ በመሙላት ለኤጀንሲው ማመልከቻውን ማቅረብ ይኖርበታል።

## 18. ስለማመልከቻው ሰነድ ይዘት

በዚህ መመሪያ በአንቀጽ 17 (ለ) መሠረት ለኤጀንሲው የሚቀርብ ማመልከቻ ቢያንስ የሚከተሉትን መያዝ ይኖርበታል።

ሀ. መሣሪያው የሚሰራበትን ፍሪኩዌንሲ ወይም የፍሪኩዌንሲ ባንዶች

ለ. ማስተላለፊያው የሚያወጣውን ከፍተኛ የሃይል መጠን

ሐ. የመሣሪያውን ዓይነትና ሰሪው

መ. የአንቴናውን ዓይነት

ሠ. ሲስተሙ (መሣሪያው እና አጠቃላይ የሥራው እንቅስቃሴ) የሚገኝበት ሥፍራ

## 19. የቴክኒክ ብቃት ማረጋገጫ የተሰጠው የስኘሬድ ስፔክትረም መሣሪያ ባለይዞታ ግዴታዎች

ለስፐሬድ ስፔክትረም መሣሪያው የቴክኒክ ብቃት ማረጋገጫ የተሰጠው ሰው፡-

ሀ. የዚህን መመሪያ ድንጋጌዎች ማክበር አለበት።

ለ. የስኘሬድ ስፔክትረም መሣሪያውን አገልግሎት በተመለከተ ኤጀንሲው ለሚያቀርባቸው ጥያቄዎች ትክክለኛውን መረጃ ሳይዘገይ መስጠት ይኖርበታል።

ሐ. በዚህ መመሪያ ከተወሰነው የሃይል መጠን በላይ ማጉላት ወይም የሃይል መጠኑን መጨመር አይችልም።



www.chilot.me

## 20. <u>የቴክኒክ ብቃት ማረጋገጫ አለማግኘት ስለሚያስከትለው ሃላፊነት</u>

ለስፕሬድ ስፔክትረም መሣሪያው ከኤጀንሲው የቴክኒክ ብቃት ማረጋገጫ ያላገኘ ሰው በዚህ መመሪያ አንቀጽ 28 ላይ በተመለከቱት አግባብነት ባላቸው ሕጎች መሠረት በወንጀል ሃላፊነት ተጠያቂ ይሆናል። መሣሪያውም በኤጀንሲው ይወረስበታል።

# <u>ክፍል ሦስት</u>

# <u>የኤጀንሲው ስልጣን ተግባርና ኃላፊነት</u>

## 21. <u>ሥልጣን፣ ተግባርና ኃላፊነት</u>

አግባብነት ባላቸው ሕጎች ለኤጀንሲው የተሰጡት ሥልጣን፣ ተግባርና ኃላፊነቶች እንደተጠበቁ ሆነው ኤጀንሲው በዚህ መመሪያ መሠረት የሚከተሉት ሥልጣን ተግባርና ኃላፊነቶች ይኖሩታል።

ሀ. በዚህ መመሪያ ውስጥ የተመለከቱት ተፈላጊ ሁኔታዎች እስከተሟሉ ድረስ ኤጀንሲው የግል ሬዲዮ መገናኛ ጣቢያ ወይም ሬዲዮ መገናኛ መሣሪያ ባለይዞታ ለመሆን፣ ለመትከል ወይም ለማካሄድ ፈቃድ ለሚጠይቁ አመልካቾች ፈቃድ ይሰጣል።

ለ. ኤጀንሲው ለስፕሬድ ስፔክትረም መሣሪያ የቴክኒክ ብቃት ማረጋገጫ ይሰጣል።

ሐ. ኤጀንሲው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (ሀ) ላይ በተመለከተው መሠረት ፈቃድ ሲሰጥ ፍሪኩዌንሲም ይመድባል።

መ. በዚህ መመሪያ ድንጋጌዎች መሠረት ኤጀንሲው ፈቃድ ለማገድ ወይም ለመሰረዝ ይችላል።

ሠ. የጊዜያዊ ፈቃድ አመልካቾች በዚህ መመሪያ ላይ የተመለከቱትን ተፈላጊ ሁኔታዎች አሟልተው በቀረቡ ጊዜ ኤጀንሲው ጊዜያዊ ፈቃድ ይሰጣል።

ረ. የኤጀንሲው ኢንስፔክተሮች የሬዲዮ መገናኛ መሣሪያ መኖሩን በበቂ ሁኔታ ሲያምኑ በሥራ ሰዓቶች ለመግባትና ምርመራ ማድረግ ይችላሉ።



www.chilot.me

ሰ. ማናቸውም ፈቃድ ወይም ጊዜያዊ ፈቃድ ያለው የሬዲዮ መገናኛ ጣቢያ ይህን መመሪያ በሚፃረር ሁኔታ በማንኛውም ሰው እጅ ጥቅም ላይ ውለው ሲገኙ የሬዲዮ መገናኛ ጣቢያውን ሥራ ለማገድ ኤጀንሲው ጣቢያውን ወይም ተገቢ መስሎ ያገኘውን የጣቢያውን ክፍሎች ለማሸግ ይችላል፡፡

ሸ. ከኢንተርፈረንስ ነፃ የሆነ የሬዲዮ መገናኛ አገልግሎት መኖሩን ለማረጋገጥ ኤጀንሲው በግል ሬዲዮ መገናኛ ጣቢያዎች ላይ ምርመራ ለማካሄድ ይችላል፡፡

ቀ. ከኢንተርፈረንስ ነፃ የሆነ የሬዲዮ መገናኛ አገልግሎት እንዲኖር ለማስቻል ኤጀንሲው የተመደበን ፍሪኩዌንሲ ለመቀየር ይችላል፡፡

በ. በሕግ መሠረት ካልሆነ በስተቀር ኤጀንሲው ፈቃዱን በተመለከተ የባለፈቃዱን ማናቸውም መረጃዎች ለሌላ ሦስተኛ ወገን አይሰጥም፡፡

ተ. የዚህን መመሪያ ድንጋጌዎች በአግባቡ ሥራ ላይ ለማዋል የኤጀንሲው ሠራተኞች ኃላፊነት አለባቸው፡፡

# ክፍል አራት

# የሬዲዮ ምስጢር፣ የአደጋ ጊዜ ጥሪ እና ኢንተርፈረንስ

## 22. የሬዲዮ ምስጢር

ሀ. ማንም ሰው የሬዲዮ መገናኛን ተጠቅሞ በሚያደርጋቸው ግንኙነቶች ላይ የማይጣስ መብት አለው፡፡

ለ. ማንም ሰው ለራሱ ወይም ለህዝብ ያልተላለፈ መልዕክት ቢቀበል ይህን መልዕክት መቅረጽ፣ ወይም ለሌላ ሰው መግለጽ ወይም መልዕክቱ ይዘት ወይም ስለመልዕክቱ ያለውን እውቀት ለግል መጠቀሚያው ማዋል አይገባውም፡፡



www.chilot.me

## 23. የአደጋ ጊዜ ጥሪ

ሀ. አንድ በሬዲዮ መገናኛ መሣሪያ የሚጠቀም ሰው የአደጋ ጊዜ ጥሪ መልዕክት መኖሩን ባወቀ ጊዜ መልዕክቱ በሚጠይቀው መሰረት በአስቸኳይ ተገቢውን እርምጃ መውሰድ የሚኖርበት ሲሆን እንዲሁም የሚቻል በሆነ ጊዜ የአደጋ ጊዜ ጥሪ መልዕክት ማስተላለፍ አለበት፡፡

ለ. አንድ የሬዲዮ መገናኛ መሣሪያ በሥራ ላይ ሳለ በአደጋ ጊዜ ጥሪ መልዕክት የማስተላለፍ ሥራ ላይ ኢንተርፌረንስ በሚፈጥር ጊዜ የዚህ ሬዲዮ ሥራ ወዲያውኑ እንዲቋረጥ መደረግ አለበት፡፡

## 24. ኢንተርፌረንስ የተከለከለ ስለመሆኑ

ሀ. ማንም ባለፈቃድ ያልተፈቀደለትን ፍሪኩዌንሲ፣ የመጠቀሚያ ጊዜ፣ ሞጁሌሽን ቴክኒክ ወይም ሌላ ዘዴ በመጠቀም በአግባቡ ፈቃድ ባገኙ ሌሎች ተጠቃሚዎች ላይ ኢንተርፌረንስ ሊፈጥር አይገባውም፡፡

ለ. ማናቸውም የኤሌክትሪክ ነክ ወይም ኤሌክትሮኒክ መሣሪያዎች ባለቤት በሬዲዮ መገናኛ አገልግሎቶች ወይም በአግባቡ ፈቃድ ባገኙ ተጠቃሚዎች የመገናኛ ሥራ ላይ ኢንተርፌረንስ መፍጠር አይኖርበትም፡፡

ሐ. በዚህ መመሪያ ላይ የተጠቀሱትን ለስፐሬድ ስፐሬክትረም መሣሪያዎች አገልግሎት የሚውሉ የፍሪኩዌንሲ ባንዶች ለኢንዱስትሪ፣ ለሳይንሳዊ፣ ለህክምና ወይም ለሌሎች አነስተኛ ሃይል ላላቸው የመጠቀሚያ መሣሪያዎች አገልግሎት ጥቅም ላይ ሊውሉ ይችላሉ፡፡ በእነዚህ ባንዶች ውስጥ የሚሰሩ የሬዲዮ መገናኛ አገልግሎት ተጠቃሚዎች ኢንተርፌረንስ ቢደርስባቸው እንደ ኢንተርፌረንስ አይቆጠርም፡፡

## 25. የኢንተርፌረንስ ምርመራና ቁጥጥር

ሀ. ኤጀንሲው በኢንተርፌረንስ ጉዳይ የሚቀርቡ አቤቱታዎችን መርምሮ ውሳኔ ይሰጣል፡፡



www.chilot.me

ለ. ሌሎች ሊጠቀሱ የሚችሉ ነጥቦች መቅረባቸው እንደተጠበቀ ሆኖ በጽሑፍ የሚቀርቡ አቤቱታዎች ቢያንስ የሚከተሉትን ጉዳዮች ማመልከት ይኖርባቸዋል፡

i. ኢንተርፌረንሱ የተፈጠረበትን ቀንና ሰዓት
ii. የኢንተርፌረንሱ ወይም ጣልቃ ገብነቱ ዓይነት
iii. የኢንተርፌረንሱ የድግግሞሽ ሁኔታ ወይም ኢንተርፌረንሱ የሚፈጠርበት የተወሰነ ጊዜ ካለው ይኸው ጊዜ

ሐ. በቴሌኮሙኒኬሽን መሣሪያዎች፣ ጣቢያዎች፣ ኔትወርክ ወይም ሲስተም ወይም የሬዲዮ መገናኛዎች ላይ ኢንተርፌረንስ ወይም ጣልቃገብነት የፈጠረ ወይም ፈጥሯል ተብሎ የተጠረጠረ የኤሌክትሪክ፣ የኤሌክትሮኒክ ወይም የሬዲዮ መገናኛ መሣሪያ ባለንብረት፣ ባለፈቃድ ወይም ተጠቃሚ ኢንተርፌረንሱ በመሣሪያው ስለመፈጠሩ የሚያጣራው ኢንስፔክተር መሣሪያውን እንዲፈትሽ የመፍቀድ ግዴታ አለበት፡፡

መ. ኤጀንሲው በቴሌኮሙኒኬሽን መሣሪያዎች፣ ጣቢያዎች፣ ኔትወርክ ወይም ሲስተም ወይም የሬዲዮ መገናኛዎች ላይ በአንድ የኤሌክትሪክ፣ ኤሌክትሮኒክ ወይም የሬዲዮ መገናኛ መሣሪያ አማካኝነት ኢንተርፌረንስ ወይም ጣልቃገብነት የተፈጠረ መሆኑን ካረጋገጠ የኤሌክትሪክ፣ ኤሌክትሮኒክ ወይም የሬዲዮ መገናኛ መሣሪያው ባለንብረት፣ ባለፈቃድ ወይም ተጠቃሚ ከዚህ በታች ከተመለከቱት ውስጥ አንዱን ወይም ሌላውን በራሱ ወጪ እንዲፈጽም ለማዘዝ ይችላል፡፡

i. ኢንተርፌረንሱን ወይም ጣልቃገብነቱን ሙሉ በሙሉ እንዲያስወግድ ወይም እንዲቀንስ ተገቢውን እርምጃ እንዲወስድ፤
ii. በመሣሪያው ላይ ያለውን ብልሽት ወይም ተገቢ ያልሆነ አሠራር እንዲያስተካክል፤
iii. የመሣሪያውን የአገጣጠም ሁኔታ እንዲቀይር ወይም እንዲያስተካክል፤
iv. መሣሪያው ጥቅም ላይ እንዳይውል እንዲያደርግ

ሠ. በዚህ አንቀፅ በንዑስ አንቀጽ (መ) የተመለከቱትን እርምጃዎች የእያንዳንዱን ሁኔታ አግባብነት ከግምት ውስጥ በማስገባት ኤጀንሲው በሚወስነው ጊዜ ውስጥ እንዲፈፀሙ ለማድረግ ይችላል፡፡


www.chilot.me

ረ. ኤጀንሲው ከላይ በንዑስ አንቀጽ (መ) እና (ሠ) የሰጣቸውን ትዕዛዞች ባለፈቃዱ ሳያከብር የቀረ እንደሆነ ኤጀንሲው በሚሰጠው የጽሑፍ ማስታወቂያ መሠረት ፈቃዱን ለማገድ ይችላል፡፡

ሰ. አንድ የኤሌክትሪክ ወይም ኤሌክትሮኒክ መሣሪያ ባለንብረት ኤጀንሲው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (መ) እና (ሠ) የሰጣቸውን ትዕዛዞች ሳያከብር የቀረ እንደሆነ ኤጀንሲው መሣሪያው እንዳይተከል ወይም ሥራ ላይ እንዳይውል ለማገድ ይችላል፡፡

ሸ. የኢንተርፈረንስ ችግር የተፈጠረው በሁለት የአንድ ፍሪኩዌንሲ ባለፈቃዶች መካከል ከሆነ ኤጀንሲው ከሁለቱ ባለፈቃዶች ዘግይቶ የፍሪኩዌንሲውን ምደባ ላገኘው ባለፈቃድ ነፃ የፍሪኩዌንሲ ስፔክትረም መኖሩን አረጋግጦ አዲስ ፍሪኩዌንሲ ይመድብለታል፡፡ ከሁለቱ ባለፈቃዶች መካከል ቀድሞ ከኤጀንሲው የፍሪኩዌንሲ ምደባ ያገኘው ባለፈቃድ በያዘው ፍሪኩዌንሲ የመጠቀም መብቱ ይጠበቅለታል፡፡

# ክፍል አምስት

# ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

## 26. አባሪዎች

ከዚህ መመሪያ ጋር ተያይዘው የሚገኙ አባሪዎች የዚህ መመሪያ አንድ አካል እንደሆኑ ተደርገው ይቆጠራሉ፡፡

## 27. የተሻሩ መመሪያዎች

ይህ መመሪያ ከመውጣቱ በፊት በሥራ ላይ የነበሩ ስለግል ሬዲዮ መገናኛ ጣቢያዎች የወጣ ደንብ ፒ-9 ከነማሻሻያው እና ሌሎች በልማድ ሲሰራባቸው የቆዩ አሠራሮች ተሽረው በዚህ መመሪያ ተተክተዋል፡፡



www.chilot.me

28. <u>ስለጥፋትና ቅጣት</u>

አግባብነት ያላቸው የአዋጅ ቁጥር 49/1996 (እንደተሻሻለው) እና ሌሎች ድንጋጌዎች ከግል የሬዲዮ መገናኛ ጣቢያዎችና መሣሪያዎች ጋር በተገናኘ በሚፈፀሙ ጥፋቶችና ቅጣቶች ላይ ተፈፃሚነት ይኖራቸዋል፡፡

29. <u>ስለማሻሻል</u>

ኤጀንሲው አስፈላጊ ሆኖ ባገኘው በማናቸውም ጊዜ ይህን መመሪያ ለማሻሻል ይችላል፡፡

30. <u>መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህ መመሪያ ከጳጉሜ 1 ቀን 1997 ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

አዲስ አበባ ጳጉሜ 1 ቀን 1997 ዓ.ም

**እሸቱ ዓለሙ**

**ዋና ሥራ አስኪያጅ**

**የኢትዮጵያ ቴሌኮሙኒኬሽን ኤጀንሲ**



www.chilot.me

የኢትዮጵያ ቴሌኮሙኒኬሽን ኤጀንሲ

አባሪ II

# ለስፕሬድ ስፔክትረም መሣሪያ የቴክኒክ ብቃት ማረጋገጫ መጠየቂያ ቅፅ

ቁጥር ____________

የአመልካቹ ስም ____________________

ዜግነት ____________________

አድራሻ ____________________

የመልዕክት ሣጥን ቁጥር ____________________ የስልክ ቁጥር ____________

የስፕሬድ ስፔክትረሙ መሣሪያ አገልግሎትና ጥቅም ____________________

**የስፕሬድ ስፔክትረሙ መሣሪያ ዝርዝር**

| የሰራው ድርጅት | ሞዴል | የሚጠቀምበት ፍሪኩዌንሲ | የአንቴናው ዓይነት | ጉልበት | የሴሪ ቁጥር | ብዛት |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | | |
| | | | | | | |
| | | | | | | |
| | | | | | | |
| | | | | | | |
| | | | | | | |
| | | | | | | |
| | | | | | | |
| | | | | | | |

**የስፕሬድ ስፔክትረሙ መሣሪያ አገልግሎት የሚሰጥበት ሥፍራ**

| ክልል | ወረዳ | ቀበሌ | የቤት ቁጥር |
|---|---|---|---|
| | | | |
| | | | |
| | | | |
| | | | |
| | | | |
| | | | |
| | | | |

. . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . .

ሥፍራ ቀን ፊርማና ማኅተም

www.chilot.me

4.1.5 £X«é© L å}Šîb¿ L QV¦ EM^L»r ˆ¿«éuG E†î¯¿\é'å £ÒAåÙ M L GŠu@ ŠM L GŠu 'å ¶Y £šéC L L V¦ †mV †¿– £D}'å £Ôg– M L GŠu ቅዕ pOGs~ pÔYOlr L iTn †Elr:: /ቅፀ·ን Š†î¯¿\é'å Ôg– L^Á "~ ŒÙG ¦EŒÙ¦ M·,r ¨uFG::/

## 4.2 £X–© »lé¦ £oq œ'å'åY ¼¦h

4.2.1 £X«é© »lé¦'å¿ 'ª EîF oq EM›'Y £Ôg– M L GŠu& M L GŠu 'åN œ'å'U ¦^ÔEµlr¿ NŒ¿¦r& £M›'Ylr¿ oq ˆ~ l†«é\å oq £Mj¨lr¿ µéšî L·EÒ †Elr::

4.2.2 £X«é© »lé¦'å 'ª pbŠY‹V F¨ £M›'Y ŠD} l4.1.3 F¨ £pµEÐ'å L T±::

## 4.3 £X–© Ôg– ˜–Qr

4.3.1 £Ôg«è¿ ‹Y–

4.3.2 pµlé £D}'å¿ —L q" £ÙVŠå"¿\é ŒÙ¦::

# 5/ †MpZv

## 5.1 †ér©É¦'å¦¿ ŠD}å

5.1.1 £L q'f¦ ‹Y–&

5.1.2 £Lµ~ƒ L QV¦'å¿ £MµGÒ pŒ}‹G nZ`Y &

5.1.3 Š6'Y '«éC £p}]'å¿ †¿– µåY– Ús ·WÙ&

5.1.4 £X–© ‰,XpY}r /£†MpY ‰,XpY}r/ \YpÖŠîr M^T±&

5.1.5 £Gªr \YpÖŠîr&

5.1.6 £†MpY Ôg– ˆ¿«é\¼ E†î¯¿\é'å £ÒAåÙ M L GŠu::

## 5.2 £'åÃ †µY šîµøv ŠD}å

5.2.1 £·E\lå L q'f¦ '¨N Ü^ÞYp¿ ŠL¯LV¦'å †Wr µÒ Û ¶Y &



www.chilot.me

5.2.2 £L V¦ Ôg− &

5.2.3 £EîF †µY £†MpY X−© Ôg− ‹E'å Ôg«è¿ &

5.1.4 Š6 'Y '«éC £p}]'å¿ †¿− µåY− £†LG‹t Ús ·WÙ::

5.1.5 £†MpY Ôg− ˆ¿«é\¼ E†î¯¿\é'å £ÒAåÙ MLGŠu::

## 5.3 £X−© Ôg− ˜−Qr

5.3.1 £Ð~ Lq'f¦ /Ü^ÞYr&

5.3.2 £'åÃ †µY šî¶ ŠD} £Ð~ £L V¦ Ôg− MiTn &

5.3.3 pµlé'å¿ —Lq" £ÙVŠå"¿\é ŒÙ¦::



www.chilot.me